ደንብ እና መመሪያዎች

**1.** ዐውድ እና ዓላማ

ስትሪም አክስለሬተር በውሃ እና ንፅህና ዘርፍ ለተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተስማሚ የሆነ የእድገት ካፒታል እና የንግድ ድጋፍ ስራዎችን በማመቻቸት፣ አገልግሎቶቻቸውን ለአዳዲስ ደንበኞች እንዲያስፋፉ የሚረዳ መርሃ ግብር ነው። መርሃ ግብሩ እምቅ አቅም ያላቸውን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ውስጥ ካሉ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት ጋር በማገናኘት እና የምክር አገልግሎት በመስጠት ድጋፍ ለማቅረብ ያለመ ነው።

አይስአዲስ ይህን መርሃ ግብር Aqua for All እና Fair & Sustainable ጋር በመተባበር ተግባራዊ እያደረገ ነው።

**2.** የማስታወቂያ ስራዎች

አጋሮች የመርሃ ግብሩን ተሳታፊዎችን እንዲሁም የተቀበሏቸውን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ በድረገጻቸው ላይ እና [አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ሁኔታ] በሌሎች የማስተዋወቂያ ጽሑፎች ላይ የማተም መብታቸው የተጠበቀ ነው። ተሳታፊዎች በተሳትፏቸው በማስተዋወቂያ እንቅስቃሴዎች፣ ዝግጅቶች እንዲሁም ጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛና ዝግጁ እንደሚሆኑ፤ በተጨማሪም አዘጋጆቹ የተሳታፊዎችን ስም፣ ፎቶግራፎች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን በሁሉም የሚዲያ መረቦች ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ ለህዝብ ይፋ ማድረግ እንደሚችሉ ይስማማሉ።

**3.** የተሳትፎ ቅድመ ሁኔታዎች

ስትሪም አክስለሬተር በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ ያሉ ነባራዊ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል የፈጠራ ሀሳብ ወይም ምርት ላላቸውና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ድርጅቶች ወይም ቡድኖች ነፃ እና ክፍት የሆነ መርሃ ግብር ነው።

ተሳታፊዎች ለተሳትፎ ብቁ ለመሆን በማመልከቻው ቀን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፦

- በውሃና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያላቸው፣
- ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ እና የተቋቋሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድና ማስረጃ ያላቸው፣
- ዝቅተኛው የመስራቾቻቸው ዕድሜ 18 ዓመት የሆነ፣ እንዲሁም
- የመርሃ ግብሩን ተግባራት ሙሉ በሙሉ መሳተፍ እና ማከናወን የሚችሉ።

የሴት ሥራ ፈጣሪዎች እና በሴቶች የሚመሩ አነስተኛ እና መካካለኛ ኢንተርፕራይዞች ተሳትፎ ይበረታታል።

በመርሃ ግብሩ በመሳተፍ፣ ተሳታፊዎች በደንብ እና መመሪያዎቹ መስማማታቸውን ያረጋግጣሉ።

**4.** ፍቺ/ትርጓሜ

ስትሪም አክስለሬተር መርሃ ግብር በውሃና ንፅህና ዘርፍ ለተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ክፍት ነው። የውሃና የንፅህና መጠበቂያ  አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ንፅህና ዘርፍ ውስጥ የሚሰሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ያካትታሉ። እነዚህ ተቋማት በአብዛኛው የሚያተኩሩት ከውሃ አቅርቦትና ከንፅህና አጠባበቅ ጋር የተያያዙ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ነው። የውሃ አቅርቦት፣ የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና አጠባበቅ ጉዳዮችን ለመፍታት [በተለይም አገልግሎቱ በሌለባቸው ማህበረሰቦች እና በማደግ ላይ ባሉ ክልሎች] የንፅህና መጠበቂያ አቅራቢዎች ጉልህ ሚናን ይጫወታሉ።

ይህም በሚከተሉት ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ያካትታል፦

- የውኃ አቅርቦት ስርዓት እና የጉድጓድ ቁፋሮ ልማት፣
- የውኃ አቅርቦት ስርዓት ሥራ እና ጥገና፣
- የቤት ውስጥ ውሃ ማጣሪያ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማከማቻ፣
- የማህበረሰብ የውሃ ማጣሪያ ስርዓቶች፣
- የዝናብ ውሃ ማከማቻ፣
- የውሃ ሀብት አስተዳደር፣
- የመጸዳጃ ቤት ግንባታ (የግል እና የህዝብ);
- የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ (ግንባታ፣ ጥገና፣ ታዳሽ ኃይል ወዘተ.)

## 5. የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ

የስትሪም አክስለሬተር መርሃ ግብር ማመልከቻን የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ግንቦት 19፣ 2016 ዓ.ም ነው።

ማመልከቻዎችን የምንረከበው ከጎን በተጠቀሰው ቅጽ ብቻ ነው (እባክዎ http://iceaddis.com/streamን ይጎብኙ)። ማመልከቻዎቹ አስፈላጊ ዝርዝር መረጃዎችን በቅጹ ማካተት አለባቸው።

የምርጫ መስፈርቶች፦

- ዘላቂነት፦ በስራ ላይ የዋለና የማደግ አቅም ያለው ዘላቂ የንግድ ሞዴል፣
- ፈጠራ፦ ዘርፉን የመቀየር አቅም ያለው የፈጠራ መፍትሄ፣
- የሚሞላው ክፍተት፦ የደንበኞችን አስተያየት፣ የሽያጭ ዕድገትን፣ ሽርክናዎችን እና የተግባር ክንውኖችን ጨምሮ ተሳታፊ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሞሉትን ክፍተት ማሳየት አለባቸው። በተጨባጭ ውጤቶች አማካኝነት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያገኙ እና አዋጭነታቸውን ሊያሳዩ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞችን ማግኘት እንፈልጋለን።
- ጠንካራ የአስተዳደር ቡድን፦ የአመራር ክህሎት ያላቸው፣ ኃላፊነት የሚወስዱ እና አዎንታዊ ባህልን ማዳበር የሚችሉ ሥራ ፈጣሪዎችን እንፈልጋለን።
- በአካባቢ የውሃና ንፅህና አጠባበቅ ስነ-ምህዳር ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ፦ መርሃ ግብሩ በተሳታፊ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርቡት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች በማኅበረሰቡና [በተለይም] አገልግሎት በሌላቸው አካባቢዎች ያላቸውን ማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ይመለከታል። የንፅህና አጠባበቅ ችግሮችን የሚፈቱ፣ ዘላቂነትን የሚያበረታቱ እና የንፁህ ውሃ እና የንፅህና መጠበቂያ ተቋማትን ተደራሽነት የሚያጎለብቱ መፍትሄዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።
- የገንዘብ መዋጮ ለማድረግ ፈቃደኛነት፦ ለመርሃ ግብሩ ወጪዎች የገንዝብ አስተዋጽዖ ማድረግ መቻልን፣ ለዕድገትና ለልማት ሀብቶችን ለማዋጣት ዝግጁነትን እና በስትሪም አክስለሬተር የቀረበውን የእሴት ሃሳብ ግንዛቤን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ እናስገባለን።
- አረንጓዴ ገፅታዎች፦ እንደ የታዳሽ ሀብቶች አጠቃቀም፣ የሃይል ቆጣቢነት፣ የቆሻሻ እና የካርበን አሻራን መቀነስ ባሉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በተሳታፊ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርቡት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ያላቸውን የአካባቢ ዘላቂነት እንገመግማለን። ለአካባቢ ጥበቃ ጠንካራ ቁርጠኝነት እና አረንጓዴ ገፅታዎችን በመተግበር ረገድ ልምድ ያላቸው ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።
- ግልጽ የሆኑ የገንዘብ ድጋፍ ፍላጎቶች፦ አመልካቾች የሚፈለጉትን የገንዘብ መጠን፣ የገንዘቡን ዓላማ እና የሚጠበቀውን የኢንቨስትመንት ውጤትን ጨምሮ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ፍላጎቶቻቸውን በግልፅ መግለፅ ይጠበቅባቸዋል።

### 5.1 የማመልከቻ ቋንቋዎች

አመልካቾች ማመልከቻቸውን በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ማቅረብ ይችላሉ።

STREAM ACCELERATOR

**5.2** ልዩ ድንጋጌዎች

የቀረቡት ተወዳዳሪ ፕሮጀክቶች ለዳኞች ከመቅረባቸው በፊት መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆናቸው ይጣራል።

በቴክኒክ ችግሮች ምክንያት ዘግይተው ለሚቀርቡት ማመልከቻዎች አጋሮች ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም።

**6.** ምርጫ ዳኞች

የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርጫ የሚከናወነው በአጋር አካላት በተመደቡ ዳኞች ነው።

- የመጨረሻ እጩዎቹ የሚመረጡት በጥብቅ የምርጫ መስፈርቶች ነው።
- የምርጫ ዳኞች እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ባለሙያዎች ምክር እና መመሪያ የመጠየቅ መብት አላቸው። ይህም የተወዳዳሪ ፕሮጀክቶቹን ሐቀኝነት ለመገምገም እና የሶስተኛ ወገን የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የሚጥስ አለመሆኑን ማረጋገጥን ይጨምራል።
- የዳኞቹ ውይይት በሰነድ ተይዞ የመጨረሻው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል። ከዚህ ባሻገር እነዚህ ውሳኔዎች በተናጥል የሚከናወኑ ሲሆን፣ የበላይ እና ለክርክር የማይቀርቡ ናቸው።
- የምርጫ ዳኞች እና አባላት በማንኛውም የተመዘገበ ተሳታፊ ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ማንኛውንም የግል ወይም የገንዘብ ፍላጎት፣ ለስፖንሰሮች ወይም ለኮሚቴ አባላት ማሳወቅ አለባቸው። ዳኞች ከተሳታፊ ወይም ከስፖንሰር ጋር የዝምድና ወይም የገንዘብ ግንኙነት ካላቸው፣ ከተሳታፊው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከመገምገም ወይም ድምጽ ከመስጠት መቆጠብ አለባቸው።
- የመራጭ ዳኞቹ ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባል ነው።